አንዳንድ ሰው አለ
በጣም የቀለለ
ከምባጮ ከዋርካ ሚዛን ያጋደለ፡፡
ዋርካና መሰሉ ፍሬውን አፍርቶ አህዛብ ይመግባል
በእምቡጡ በአበባው መንፈስ ያስደስታል
ወይዛዝርት ጉብሎች ይመሰሉበታል
ቅጠል ስራስሩ ደዉየን ያስወግዳል
ዛፍ ዘርፈ ብዙ ነው ሁሉን ይፈዉሳል፡
የአእዋፍ ማረፊያ ጎጆ መቀለሻ
የጦጣ ጉሬዛው መከታና ጋሻ
የሰሳ ሚዳቋ መደበቂያ ዋሻ፡፡
ዛፍ ዘርፈ ብዙ ነው የማይሆነው የለ
በውብ አክናፎቹ ሁሉን የጠለለ
አንዳንድ ሰዉ አለ
ከዛፍ የቀለለ
አተኩሮ ሳዩ በጣም ሳስተዋስ፡፡
ቤት መስራት አቅቶት፤
የሰራው ፈርሶበት፤
የጊዜ ቅንቃኖች ኦና አድረገዉበት፤
ቁርና ሃሩሩ ሱፈራረቁበት፤
ሁሉም ኤጭ ብሎ፤
የለም በሉ ተብሎ፤
በር ሲዘጋበዎት፤
ከለሳ መከታ መጠጊያ ያጡለት፤
ዛፍ ጥላ ይሆናል፤
በቅጠሎቹ አክናፍ ከወጀብ ከዶፉ ፤
አለኝታ ይሆናል፤
ለደከመ ገላ ለዛለ ሰውነት ብርታት ጆባ ይሳል፡፡
ያንዳንድ ሰው ነገር ዛፍን ግኡዝ ይሳል
ይህን የሰው አጋር በለመደ አንደበት ጥሎ ለማጣጣል፡፡
ዳሩ ምን ያደርጋል እሱ ከዛፍ አንሶ፤
ድርጊቱ ኮስሶ፤
ሞራሉ ተራክሶ፤
ስብእናው በስብሶ፤
ካልኪዳን አፍርሶ፤
ማተቡን በጥሶ፤
ለኩርማን እንጀራ ወገኑን አጋልጦ፤
ባረማዊ ፍጡር ነብሰ ስጋ አስንጉጦ፤
ኑሮን ሲኦል አርጎ ባጋንንት ወረንጦ፤
ይገፋል እድሜዉን፤
ያዘግማል ጉዞዉን፤
ወንድሙን አሳምጦ፡፡
ምናባቱ ሞራል፤እህል ብቻ ይኑር፤

የምን ንጽህና ህሊናም ይታወር፤
የምን ሀቀኝነት እዉነትም  ትቀበር፤
ሞራል ገደል ይግባ ይበል ሁሉም ጥንቅር፤
ሲሆን መፈክሩ፤ ከበላሁ ከጠጣሁ፤
ሞራዬ ካበጠ ከርሴንም ከሞላሁ፤
እኔ ምን አገባኝ፤እኔ ካለው አለሁ::
እያለ ሲዘምር፤ስንኝ ሲደረድር፤
ካደመጥን ሲነግር፤ሲያስነግር፤
አይገርምም ዎይ ከቶ ያንዳንድ ሰው ነገር::
በእንትኗ ፍልስፍና መኖር ከጀመሩ፤
ያለ እንበለ ሃፍረት ምንንም ሳይፈሩ፤
እንዴት ያዳም ፍጡር ሰው ተብሎ ይጠራል፤
ግኡዝ ነው ካሉቱ፤ከዋርካ ከዝግባው አሳነስኩም ይሷል?

አድማሱ